እርምጃ መውሰድ እና እርዳታ ማግኘት

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ከሕግ ውጪና አደገኛ ነው እርስዎንና ልጆችዎን ከአደጋ ለመከላከል መውሰድ የሚችሏቸው ብዙ እርምጃዎች አሉ።

ከቤት ወስጥ ይውጡ፤ እንደዚሁም/በተጨማሪ ለፖሊስ ይደውሉ

በተጨማሪ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥምዎት ከአደጋ እራስዎን በደህና ለማውጣት አስቀድመው ይዘጋጁ እቅድ ያውጡ፡

እርዳታ ከሰለባዎች መጠለያ፤ ከህት ላይን እና ከአድቮኬቶች/ደጋፊዎች ማግኘት ይችላሉ።

ከቤት ውስጥ ይውጡ

- ጥቃት በሚደረግብዎ ሰዓት የሚቻል ከሆነ ከቤት ውስጥ ይውጡ ከምታምኑአቸው ጎረቤት ጓደኛ ወይም የቤተሰብ አባል እርዳታ ይጠይቁ
- 911ይደውሉ ወይም ልጆችዎን 911እንዲደውሉ ይጠይቁ.
- ከቤት ውስጥ መውጣት የማይችሉ ከሆነ ከወጥ/ከማዕድ ቤት፤ ከመጸዳጃ ቤት፡ ከመኪና ማቆሚያ እና ሌላ አደገኛ ከሆኑ ክፍሎች ወይም ቦታዎች ይውጡ
- ለእርዳታ ይጣሩ፤ ጎረቤት ሊሰማዎት ይችላል።

እነዚህን እርምጃዎች ለመውሰድ አስቀድመው እቅድ ማውጣት ይችላሉ

አደጋ ላይ ከሆኑ በፍጥነት 911 ይደውሉ

ፖሊስ -

የቤት ውስጥ ግጭትን/ሁከትን በሚመለከት እርስዎን ለመርዳት እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ ለማስረዳት ፖሊሶች እውቀት አላቸው፤ ጉዳዮን በጥብቅ ይይዙታል። አደጋ ላይ ነኝ ብለው የሚያስቡ ከሆነ በፍጥነት ወደ ፖሊስ ይደውሉ አይዘግዩ. በሚደውሉበት ወቅት ለሚናገሩት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲቀርብሎት ይጠይቁ; ፖሊስ ይህን ለማድረግ ግዴታ አለበት;
ፖሊስ ሲመጣ የኢምግሬሽን ጉዳዮን በሚመለከት ምንም ጥያቄ አይጠይቆትም።
ሀትላይን - ጭንቀት ላይ ከሆኑ፡ ምክር የሚፈልጉ ከሆነ ወይም ከሰው ጋር መነጋገር የሚፈልጉ ከሆነ ሀትላይን ሊረዳዎት ይችላል ሀትላይኑ በሚናገሩት ቋንቋ እርዳታ ሊያገኙ ወደሚችሉበት መገልገያዎች አመላክቶዎ እርስዎና ልጆችዎ መጠለያ ቦታ እንዲያገኙ ይረዳዎታል በተጨመሪ ከአድቮኬት ጋር ያገናኝዎታል አድቮኬት ከዚህ በኋላ ምን እንደሚየደርጉ እቅድ ለማውጣት ያግዝዎታል ሀትላይን መረጃ ይሰጥዎታል ጉዳዮንም በሚስጥር ይጠብቃል።

አደጋ ላይ ከሆነ ያሉት 911 ይደውሉ

መጠለያ - ለእርስዎና ለልጆችዎ ካአደጋ ነጻ የሆነ ማረፊያ ቦታ
እቤትዎ ውስጥ መኖር አደገኛ ከሆነና መውጣት ከፈለጉ ለጊዜው ለእርስዎና ለልጆቸዎ መጠለያ መሄድ ጥሩ አማራጭ ይሆናል።

አደጋ ላይ ከሆነ ያሉት 911 ይደውሉ

አድቮኬት/ደጋፊዎች - በእርስዎ በኩል ያለ ሰው

አድቮኬት ድጋፍ ይሰጣል፡ የወደፊት ኑሮዎን በሚመለከትና በደህንነትዎ ምርጫ መገንቢያ ወቅት ይረዳዎታል አድቮኬቷ እንደ እርስዎ ዓይነት ጉዳይ ካላቸው ሰዎች ጋር የመሥራት ልምድ አላት/ው. አድቮኬት የሕግ መብትዎን ይገልጽሎታል፤አድቮኬት ያኢርሶን ሀሳብ ያዳምጣል፤ ስለ ልምድዎ ይናገራል፤ ከአደጋ ነጻ የሆነ ኑሮ እንዲመሠርቱ አስፈላጊውን እርዳታ ይሰጣል።

አደጋ ላይ ከሆነ ያሉት 911 የደውሉ

ከፖሊስ እርዳታ ማግኘት

ከሚጎዳዎና ከሚያስፈራራዎ ሰው የመከላከል መብት አሎት ብቻዎን አይደለም ያሉት ፖሊስ ይረዳዎታል፣

911 ሲደውሉ

- ከዚህ በታች የተጠቀሱትን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ፦ትክክል የቤት አድራሻ፤ለምን ጉዳይ እንደደወሉ/ምን እንደሆነ ገለጻ፤ ድርጊቱ መቼ እንደሆነ፤ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ስም፤ የትውልድ ቀን፡ የመኪና ታርጋ ቁጥር፤ ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ምን እንደሚመስል የፀጉር ቀለም፤የቆዳ ቀለም፤ እድሜ፤ቁመቱ፤ክብደት።
- ኦፐሬተሯ ፖሊስ ወደ ቤትዎ ትልካለች፡ ፖሊስ ወዲያው ሊደርስ አይችልም ይሆናል፡ እስከዛ ድረስ ግን ደህንነትዎን ያረጋግጡ በተቻለ መጠን ካደጋ ተጠበቁ።

የኢምግሬሽን ስታተስዎ የተስተካከለ ይሁንም አይሁን

- ከሚያስፈራራዎና ከሚጎዳዎ ሰው ለመከልከልና ለመጠበቅ 911 ደውለው የፖሊስ እርዳታ መጠየቅ መብት አሎት
- ፖሊስ ይረዳዎታል ይከላከሎታልም
- የከተማው ፖሊስ ስለ የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ጉዳዮን ለኢምግሪሽን አያስታውቅም ( ሆኖም ኢምግሬሽን በፍርድቤት ሂደት ወቅት ሊነገረው ይችለላል) ስለ ኢምግሬሽን ስታተስዎ ፖሊስ ቢጠይቅዎ መመለስ እንደማይፈልጉና ጠበቃ ማናገር እንደሚፈልጉ ይናገሩ።

እንግሊዘኛ መናገር የማይችሉ ከሆነ

- በሚደውሉበት ግዜ የሚናገሩትን ቋንቋ ስም ይንገሩ፤ የ911 ኦፐሬተሯ የእርስዎን ቋንቋ የሚናገር አስተርጓሚ በስልክ ትገናኛለች
- ከዛ በኋላ ከኦፐሬተሯና ከአስተርጓሚ ጋር ይነጋገራሉ።

ፖሊስ ሲደርስ/ሲመጣ

- በቤት ውስጥ መሣሪያ- ሽጉጥ ካለ ለፖሊሱ ያለበትን ቦታ ይንገሩ
- ጉዳት በአካልዎ ላይ ደርሶ ከሆነ ለፖሊሱ ቁስልዎን፤ስብራትዎን ያሳዩ
- የፕሮቴክሽን ኦርደር/ገደብ ካልዎት ለፖሊሱ ይንገሩ ኮፒውንም ያሳዩ።

ፖሊሱ

- እርስዎን እና የኑሮ ጓደኛዎን/ወይም ጉዳት ያደረሰብዎን ሰው ይለያያል

- ጠይቀው ከሆነ አስተርጓሚ ያመጣል
- እያነጋገጋችሁን ጥያቄ ይጠይቃል
- ስለ ሆነው ነገር የተቻለውን ያህል መረጃ ይሰበስባል (የኑሮ ጓደኛዎ ከዚህ በፊት ጎድተዎ ወይም አስፈራርተዎ ከሆነ ይህ አስፈላጊ መረጃ ስለሆነ ለፖሊሱ ይንገሩ)
- ደህና መሆንዎን ለማረጋገጥና ፕሮቴክሽን ኦርደሩን/የፍርድቤት ማሳገጃ ለማስከበር ከእርስዎ ጋር ትንሽ ይቆያል
- ሕጋዊ መብትዎን ያስረዳዎታል
- በአካባቢዎ ስለ አሉ መጠለያዎች እና ሌሎች አገልግሎቶች መረጃ ይሰጥዎታል
- ከቤት መውጣት ከፈለጉ በደህና እንዲወጡ ይረዳዎታል፤ ወደ ደህና ቦታ የሚሄዱበትን መጓጓዣ እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

ፖሊሱ እርስዎንና አጥቂዎን ለማስታረቅ መሞከር የለበትም

<u>እንግሊዘኛ ለመናገር ችግር ካለብዎ</u>

- የሚያምኑት ሰው እንዲያስተረጉምሎ ያምጡ (የጎዳዎት ሰው፤ ልጅዎ፤የጎዳዎ ሰው ጓደኛ ወይም ዘመድ መሆን የለበትም)
- ፖሊሱ በስልክ አስተርጓሚ ደውሎ ሊያገናኛ ይችላል
- በራስዎ ቋንቋ ስለ ሆነው ሁኔታ በዝርዝር ጽፈው ለፖሊሱ ከሪፖርቱ ጋር እንዲያያይዘው/እንዲጨምረው መስጠት ይችላሉ።

<u>ፖሊስ ከመሔዱ በፊት</u>

- ወንጀል ተፈጽሞዋል ብለው ካመኑ ፖሊሶቹ አጥቂውን ሰው እስር ቤት ይወስዱ ይሆናል
- የፖሊሷን/ሱን ስም፤ መታወቂያ ቁጥር፤ ከየትኛው ፖሊስ ጣቢያ እንደሆነ እና የስልክ ቁጥር መጠየቅ ይችላሉ የተሰጥዎን መረጃ ይጻፉ ወይም የፖሊሷን/ሱን ቢዝነስ ካርድ ይቀበሉ
- የጉዳዩን ቁጥር ይጠይቁና ይጻፉ።

ፖሊስ/ሶች ከሄዱ በኂላ

- ፖሊሶች አጥቂውን ካሠሩት፤ አጥቂው ከጥቂት ሰዓቶች በኂላ ሊፈታ ይችላል ወይም ጥቂት ቀናቶች ሊቆይ ይችላል ወይም ረጅም ጊዜ ሊታሠር ይችላል
ቫይን ላይ ከተመዘገቡ አጥቂው ሲፈታ የቴሌፎን መልዕክት ሊቀበሉ ይችላሉ ቫይን የኮምፒተር ቴሌፎን ሲስተም ነው (ግልጋሎት የሚሰጠው ለኪንግካውንቲ እስር ቤት ብቻ ነው) ለዚህ ነፃ አገልግሎት መመዝገብ ከፈለጉ 1-877-425-8463 በመደወል ከአድቮኬት ጋር ለመናነር ይጠይቁ.
- ፖሊሶቹ መብትዎን በትክክለኛው መንገድ ያላከበሩ ከመሰልዎ ለፖሊሶቹ አዛዥ ቅሬታዎን ያቅርቡ ይህንን ማድረግ መብትዎ ነው አቤቱታዎ መሸሽልን ሊያመጣ ይችላል፤ ሌሎችንም ይረዳል።